# ኦባንግ ሜቶ በሎንዶን

ከወንድሙ መኰንን

እሑድ ኅዳር ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም (23 November 2008)፣ ኢትዮጵያዊው የጋምቤላ ተወላጅ፤ በሎንዶን 2A ሊቶስ መንገድ በሚገኘው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ በብሪታኒያ አዳራሽ ከተለያዩ ቦታ የመጡትን ኢትዮጵያውያን አግኝተው በሰፊው አነጋግረዋል። እኚህ ታዋቂ የሰበዓዊ መብት ተሟጋች፣ የኢትዮጵያዊነትና የአንደነት ጠበቃ፣ በሚማርከውና ከልባቸው በሚፈልቀው ዕውነተኛ ኃሳብ ላይ በመመርኮዝ፣ የታዳሚውን ልብ ማርከዋል። ለማስተላለፍ የተፈለገውንም መልዕክታቸውን በሚያሳምን ሁኔታ አስተላልፈዋል። መምሸቱ ገላገላቸው እንጂ፤ ታዳሚውስ ከዚያች አዳራሽ ንቅንቅ ሳይል ስልህገሩ በሚገባ ተወያይቶበታል። ከዚህ በፊት በኢትዮጵያውያን ስብሰባ ላይ ያልተገኙት ወገኖቻችንም ተገኝተዋል። ከዚህ በፊት ተናግረው ያልተደመጡ ኢትዮጵያውያን የልባቸውን አውጥተው መናገር ችለዋል። ኦባንግ እንኳን ኢትዮጵያዊነትን ሌት ተቀን የሚሰብኩትን ወገኖችና፣ ኢትዮጵያዊነታቸው ያሳፍራቸው የነበርውን ሳይቀር በኢትዮጵያዊነታቸው እንዲኮሩ አሳምነዋቸዋል።

ለመሆኑ ምን ብለው ቢሆን ነው እንዲህ የሰውን ቀልብ መሳብ ያቻሉት። ይኸ ጸሐፊ አንዳንድ የሚያስታውሳቸውን ነገሮች፣ ካንባቢው እንደሚከተለው ያቀርባል።

ተሰብሳቢው ሕብረተሰብ የሞቱትን፣ የታሰሩትን፣ በወያኔ አፋኞች ተጠልፈው ደብዛቸው የጠፋውንና የተሰደዱትን ወገኖች በሐሊና ጸሎት ካስታወሳቸው በኋላ፤ አስተናባሪው አቶ ኦባንግን በአጭሩ አስተዋውቆ ሲቀመጥ፣ አቶ ኦባንግ መድረኩን ያዙት። እንዲህ በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ።

> “በጣም ለጋ ወጣት እያለሁ ከአገሬ ወጥቼ ብዙ ዘመን ውጭ አገር በመኖሬ የጋራ መግባቢያችን የሆነው አማርኛ ስለጠፋብኝ የፈለግኩትን ሁሉ እንደልቤ መናገር ስለማልችል በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅኩ፣ እንግሊዝኛ እየቀላቀልኩ ስናገር ይቅርታ እጥይቃለሁ፣ ሁላችሁም እንግሊዝኛ ስለምትረዱ የምለውን እንደምታዳምጡኝ ተስፋ አድርጋለሁ” አሉ።

ተሰብሳቢው ይሁንታውን ካስታወቃቸው በኋላ ንግግራቸውን ቀጠሉ። በመጀምሪያ ከማንም ጋር ቂም እንዳልነበራቸውና፤ ቂም መያዝ እንድማይችሉ ሁሉም እንድትረዳላቸው ጠያቁ።፣ ከማናችሁም ጋር ቅሬታ እንደሌላቸውም አረጋገጡ። ተሰብሳቢው ከየትኛውም ወገን ሊመጣ ይቻላል። የማንኛውም ድርጅት ሊሁን ይችላል። አቶ ኦባንግ ግን ሁሉንም የሚያዩት በአንድ ዓይን፤ በእኩልነት ነው መሆኑን አስጨበጡ።

ይኸንን አቋማቸውን ግልጽ አድርገው ካስቀመጡ በኋላ ለጥቀው የሚከተለው መመሪያ ደግሞ እንዲይዝላቸው ታዳሚውን አስገነዘቡት።

> አሁን እዝህ ፊት ለፊታችሁ ተቅምጬ እያንዳንዳችሁን ስመለከታችሁ፣ ስለ እናንተ የማውቀው ነገር ቢኖር ውስን ነው። ስማችሁን አላውቅም። ማንነታችሁን አላውቅም። ዘራችሁን ወይም ከየትኛው ብሔረሰብ እንደፈለቃችሁ የማውቀው ነገር የለም። ነገር ግን ስለሁለት ቁም ነገሮች በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። እኔና እናንተን አንድ ያደረገን አንዱ ሁላችንም እዚህ የተሰበሰብነው የሰው ልጆች፣ ሰብዓዊ ፍጥራን መሆናችንን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። ሁለተኛው ዕውነታ፣ በዕርግጠኝነት መናገር የምችለው ሁላችንም ዛሬ እዚች ጣሪያ ሥር የተሰበሰብነው በሙሉ ኢትዮጵያውያውን መሆናችንን ነው። ኢትዮጵያዊ ካልሁንክ ምን ታደርጋለህ እዚህ? ምን ታደርጊያለሽ እዚህ? ለመነሻነት በነዚህ ሁለት ዓበይት የሚያገናኙን ነጥቦች እንተማመን።

ታዳሚው ይኸንንም ጭብጥ በማያወላውል ሁኔታ እራሱን እየነቅነቀ አረጋገጥላቸው። ኦባንግ ቀጠሉ (አንዳንዱ ስማቸውን እያሳሳተ ኦባማ ያላቸውም ነበረ።)

ሰው በሰው ልጅነቱ ብቻ አንድ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። በቅርጹና በይዘቱ ሊለያይ ይችላል። አንዱ አጭር ነው። አንዱ ቀጭን ነው። አንዱ ረዢም ነው። አንዱ አጭር ነው። አንዱ ቀላ ይላል። አንዱ ጠቆር ይላል። አንድ ቀጥ ያለ አፍንጫ አለው። ሌላው ደፍጠጥ ያላል። ይኽ ሁሉ ልዩነት፣ ሰውነቱን እንደማያስጥለው በሚገባ ቋንቋ አስረዱ ቀጥለውም ደግሞ ሶስት ነጥቦችን ተራ በተራ አነሱ። መጀመሪያ ማንነቸውን አስረዱ። ቀጥለውም እንዴት ወደዚህ የሰብዓዊ መብት ትግል እንደገቡ በግልጽ አስቀመጡ። ወደፊትስ ወዴት እንደምሔዱ የትግል አቅጣጫቸውን በማያወላዳ አኳኋን አመለከቱ።

> ተውልጀ ያደግኩት ጋምቤላ በመባል በሚታወቀ ቦታ ነው። ጋምቤላ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ያ ያለምንም ማውላውል ኢትዮጵያዊ ያደርገኛል። ወላጆቼም የአኟክ ብሔረ ሰብ አባል ነበሩ። አንድ ነገር እንድትረዱልኝ የምፈልገው እኔ አኟክ ሁኜ ለመፈጠር ምርጫ አልነበረኝም። ስወለድ ዘር ሐረግ የሚባል ነገር አላውቅም ነበር። ቋንቋ አልነበረኝም። ባሕል አልነበረኝም። ኃይምኖት አልነበረኝም። አኟክነቴን አላውቀውም ነበር። ሰው፣ ሁኜ፣ ሰብዓዊ ፍጡር ግን ነበርኩኝ። በአጋጣሚ በጋምቤላ ከአኟክ ቤተሰብ ተወልድኩ እንጂ ትግራይ ውስጥ ለወለድ እችል ነበር። አኟክነቴን ያወቅኩት ከአድግኩ በኋላ፣ ሊገባኝ ሲችል ወርሼው ነው። ቋንቋውንም ተምሬ ነው። ባሕሉንም ተምሬ ነው። የአኟኩ ተወላጅ፣ ኦባንግ ልሆን የቻልኩት፣ ከቤተሰቤ፣ ከወላጆቼ፣ ከአካባቢዬ ወርሼው ነው። ያ ሁሉ የወረስኩት ግን፣ የሰው ፍጡር መሆኔን ሊያስቀረው ክቶም አይችልም። ሳድግም፣ ነገሩ በድንብ ሲገባኝም፣ ከሰውነቴ ባሻገር ኢትዮጵያዊ ነኝ። የምነገራችሁ ነገር በሙሉ ከልቤ የማምነበትን ነው። ነገር ለማሳመር ሳይሆን አምኜ የተቀበልኩትን ነው። ከጋምቤላ የተገኘሁ የሰው ልጅ ነኝ። ጋምቤላ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሚገኘው። እንግዲህ የኢትዮጵያዊነቴን ዜግነትና መብት የተቀዳጀሁት በውስጧ በመወለዴ ነው።

ታዳሚው የሚሉትን ሁሉ መረዳቱን በጭብጨባ አረጋገጠላቸው። እያንዳንዱ ፊት ላይ ይነበብ የነበረው "ቀጥሎ ምን ይሉን ይሆን የሚል ስሜት" ጉጉት ነበር። ከአገራቸው ለብዙ አመታት ወጥተው ቆይተው በአጋጣሚ ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ አገራቸውንና ዘመድ አዝማዳቸውን ለመጠየቅ እንደተመለሱ አስረዱ። ያዩት አስደነገጣቸው። የሕዝባቸው ኑሮ የባሰውኑ ወድቆ ጠበቃቸው። "ይኸን ጎስቋላ ሕዝብ ለመርዳት አንድ ነገር የበኩሌን ላድርግ" ብለው በቁርጠኝነት ተነሱ። ወያኔም ሥልጣን ላይ ወጥቶ ዲሞክራሲ አመጣሁ ብሎ ሲለፍፍ፣ ነበር። አቶ ኦባንግ ግን ለዚያ ብዙም ቦታ አልሰጡትም። ምክንያታቸውንም ሲግልጹ እምብዛም የፖለቲካው ነገር ስለማይገባቸው ነበር። እሱን ወደጎን ትተው የተጎሳቆሉትንና የባሰውኑ መሐይምነት ቀፍደዶ የያዛቸውን፣ የሚጠጣ ንጹህ ውሀ ያጡትን (ልብ በሉ ባሮን የሚያክል ወንዝ ጋምቤላን አቋርጦ ይፈሳል)፣ በቀላሉ በሚድን በሽታ ተጠቅተው፣ ከማጡ ወደ ረመጡ ወርደው የጠበቁአቸውን የጋምቤላ ሕብረተሰብ ወገናቸውንና ዘመዶቻቸውን ለመርዳት ቆርጠው እንደተነሱ አስረዱ። ቶሎ ብለውም ካናዳ ውስጥ ከሚያውቁአቸው ሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር ተነጋግው፡ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት (መያድ)፡ ለማቋቋምና ሀሳብ አውጠነጠኑ። ንድፈ ሀሳብም አውጥተው መያዱን ሕጋዊ ለማድረግ የሚመለከተው ሚኒስቴር ሹም ጋ በጠቋሚ ለማነጋገር ሄዱ። ኃላፊውን አግኝተው አነጋገሩት። እጁን ዘርግቶ "እሰየው! ተገኝቶ ነው! ና እርዳን" ይለኛል ብለው ሲጠብቁት፤ ጭራሹኑ "ለምን መያድ ለመፍጠር ፍልግክ" ብሎ የፖሊስ ጥያቄ ሲደረድርላቸው ግራ ተጋቡ። መለስ ብለውም ነግሩ ያልገባው መስሎአቸው፣ ደጋግመው ሊገባው በሚችል ቋንቋ ሕዝቡ ያለበትን አሳዛኝ ሁኔታ ልባቸው እስኪውልቅ ልያስረዱት ሞከሩ። ዓይጥ የዋጠች ድመት ይመስል፤ ዓይኑን ብቻ ቁልጭ-ቁልጭ አድርጎ፣ ተመለከታቸው። በኋላም ላይ "መያድ መመሥረት ከፈለግክ የሚፈቀድልህ ስሜን ብቻ ስንልክህ ነው። እዚያ ነው እንድትከፍት የምንፈቅድልህ" ብሎአቸው እርፍ አለ። ንድድ ብሎአቸው "ለመሆኑ ሰሜን ምን ሁኖ ነው እዚያ ሂጄ መያድ እምክፍተው" ብለው ሲጠይቁት "በጦርነት የተጎዳው ያ የአገሪቱ ክፍል ነው" ብሎ ድርቅ አለባቸው። እሳቸውም የተወለዱበትን ጋምቤላ፣ እንጂ ሰሜን የሚሄዱበት ምክኒያት ስላልታያቸው ወዲዚያ ለመሄድ አለመፈለጋቸውን እቅጩን ሲነግሩት "አዝናለሁ፤ ይቅርታ" ብሎ አሰናበትቸው። የፈለጉትን ማድረግ

አቅቶአቸው፣ በጣም እያዘኑ ወደ መጣሁበት ተመሱ። አቶ ኦባንግ ይኸንን አሳዛኝ ገጠመኝ ሲነግሩቱ፣ ተሰብሳቢው ፊት ላይ በጣም ንደትና ወያኔ ላይ ትዝብቱን እያንዳንዱ ሰው አንገቱን አንገቱን በመነቅነቅ ተረዳቸው። ላያቋርጣቸው ብቻ ሲል በጽሞና ማዳመጡን ቀጠለ።

> በፈረጀቹ አቆጣጠር ዲሰምበር 13 2003 ዓ. ም. አንድ አስደንጋጭ ዜና ደረሰን። የመንግሥት ወታደሮች የዋሁን የአኟክ መንደር በመውረር 427 ሰዎችን በአንዲት ጀምበር እንደፈጁአቸው ሰማተን ተደናግጠን። ከትንሽ ቀናት በኋላ አንድ ጓደኛዬ የ427 ሰዎች ስም ዝርዝር የያዘ ፋክስ ላከልኝ። የተገደሉት ሰውች ስም ዝርዝር ነበር። አንዳዱ የኔው ቤተሰብ አባል ነበር። ገማሹ አብሮ አደጌ ነበር። ክ427 ስም ዝርዝሮች 379 በግል የማውቃቸው የቅርብ ዘመዶቼና ወዳጆቼ ነበሩ። የማረገውን አጣሁ። ስልክ አነሳሁና ስቴት ዴፓርትመንት ደወልኩ። አንዲት ሴት አነሳችው። ስሜን፣ ማንነተን ከነገርኳት በኋላ፣ 427 ሰዎች ኢትዮጵያው ውስጥ በግፍ እንደተጨፈጨፉ ነገርኳት። "ታዲያ ምንድነው የምትፈልገው" አልችኝ። "ጭፍጨፋውን ለማቆም አንድ ነገር እንድታደርጉ ነው" አልኳት። "አፍሪካው ውስጥ ከዚያም በላይ በየቁን ይጨፈጨፋል። ምንም ልናደርግ አንችልም" ብላ ጆሮዬ ላይ ደረገመቸው። ትንሽ ቆይቼ መልሼ ደወልኩ። ያቸው ሴት አነሳች። ቶሎ ብዬ እንዳትዘጋብኝ ለመንኳት። "ምን የተለየ ነገር ልትነግረኝ ነው" አለችኝ። "ከነዚያ ከተጨፈጨፉት መሀል የዩኤስ ዜጎች አሉበት። ነገሩ ካልቆመ ሌሎች ዘጎቻችሁ ሊጨፈጭፉ ይችላሉ" አልኳት። ድምጿ ተቀየረ። አጥብቃ ጠየቀችኝ። ሌላ ሰው ቀረበ። ተቀባበሉኝ። የአንድ አምስት በትውልድ ኢትዮጵያዊ የጋምቤላ ተውላጆች፤ በፓስፖርት ግን አሜሪካውያን የሆኑትን የአምስት ሰዎች ስም ዝርዝር ከነፓስፖርት ቁጥራቸው ነገርኳቸው። አረጋገጡ። ወዲያው "ዛሬውኑ ፍልጎ-አዳኝ እስኳዳችን ጋምቤላ ገብቶ ያድራሉ" ብለው ቃል ገቡልኝ። ተመልከቱ። ሌላው መንግሥት ያልተወለደውን፣ ደንበር ለመተላለፍ ምቹ የሆነውን ፓስፖርቱን ያያዙትን ዜጎችን ለመታደግ፣ አምስትም ይሁኑ ሶስት፣ ቀራጥ እርምጃ ወስዶ ያድናቸዋል። ይኸ ነው ለዜጎቹ ሃሳቢ መንግሥት ማለት። እስቲ በዕውነት ለዕውመት እንነጋገር። የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቀለም አንድ ማጥ ውስጥ ብንገባ ያድነናል? እዚአ አዳራሽ ውስጥ ያላችሁ ወያኔዎች ስሙኝ። አዋርዳችሁናል። ኢትዮጵያዊነትን ዋጋ አሳጥታችሁአል። ይኸን ስታደርጉ አላወቃችሁትም እንጂ እራሳችሁን ነው ያወረዳችሁት።

በማለት ስሜት በተሞላበት ኦባንግ የጋምቤላን ጭፍጭፉ አስረድዱ። ቤቱ የተቀጣጠለ መሰለ። ጭብጨባው ተሰገጋባ። ታዳሚው ስሜቱ ነደደ! አቶ ኦባንግ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ወዲያው ጸጥ አለ። አቶ ኦባንግም ከዚያ በኋላ ነው ጨርቄን ማቄን ስያሉ ትግሉ ውስጥ የተዘፍቁት። የአኟኩን ጉዳይ ወደ ዓለም አቀፍ ደርጃ አድርሰው ጭፍጭፋው የዘር ማጥፋት እንደሆነ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተመራማሪዎች ማዕከል ማረጋገጫ አወጡ። እስከዛሬ ገዳዮቹ ለፍርድ ባይቀርቡም ደማቸው የመጮህ ዕድል አገኘ። በኋላ ላይ አቶ ኦባንግ ሲረዱት ላካንስ ሥራዬ ብሎ የሚጮህላቸው ጠፍቶ ነው እንጂ ሌላም ቦታ እንደዚያ ዓይነት ጭካኔ የተሞላባት ጭፍጨፋ ይካሄድ ኑሯል። እሳቸውስ ለአኟኩ ጩኹና ትንሽም ብትሆን ውጤት ተገኘች። ለአማራውስ ወንድማችው ማን ይጩኸለት? ለኦሮሞውስ ያገራቸው ልጅ በደሉን ማን ያስተጋባለት? ለሲዳማውስ? ለሶማሌውስ? ለካምባታውስ? "የለም እኔ ላኟክ ባቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያዊ ወገኔ መጮህ አለብኝ" ብለው ቆርጠው እንደተነሱ ለታዳሚው በሚጣፍጥ ቋንቋ ጥርት አድርገው አስረዱ። አሁንም ተሰብሳቢው ይኸንን አቋማቸውን መደገፉን ገለጸላቸው።

ወደ መደምደሚያው ላይ ኦባንግ ሲናገሩ፣ ኦሮሞው ለኦሮሞው ብቻ ታግሎ ነጻ ከወጣ ሌላው ነጻ እስካልወጣ ድርስ ነጻ ሊሆን አይችልም አይችልምና ብሎ አያውራ አሉ። አማራው ታግሎ የራሱን ጎሳ ነጻ ካወጣ፤ አንድም ኢትዮጵያዊ ነጻ እስካልወጣ ድረስ ነጻ ንኝ አይበል አሉ። "ለአኟክ ታግለን ነጻ ካውጣነው ሌላው ኢትዮጵያዊ ሥቃይ ሥር እስከሆነ ድርሰ ነጻ ልንሆን አንችልም" ብለው የሕዝቡን አንጀት አራሱት። ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ላይ ቁሞ ከጭቆና ቀንበር ተላቆ፣ በፍቅር፣ በአንድነት፣ በመተሳሰብ፣ በመከባበር አንድ ላይ ይሚኖርባትን ኢትዮጵያ ለማምጣት አማራጭ የሌለው የትግል ስልት መሆኑን ያለ አንዳች ማወላወል አስረዱ። የነገዋ ኢትዮጵያ አዲሱ ትውልድ በኩራት የሚወርሳት እንጂ የሚሸማቀቅባት መሆን እንደሌለባት አስረዱ። ኢትዮጵያውያን በአገራቸው አንድ

ላይ የሚኖሩባት የቤተሰብ ቤት መሆን ሲገባት፣ ቤትሰብን ከቤትሰብ አጣልቶ የሚሊያይ ኃይል መጥቶባታልና የዚህ ቤተሰብ አባል አንድ ላይ በመተባበር የተቃጣበትን በተና ከመቋቋም ሌላ ማራጭ እንደሌለው ያለአንዳች ማወላወል ጥረኢያቸውን አስተላለፉ።

የዚህንም የአንድ የቤትሰብ ቤትነት ምሳሌ ሲያቀርቡ እንዲህ አሉ።

> ኢትዮጵያን እንደ አንድ ቤት ውሰዱት። እሳት ተነስቷል እንበል። እኔ እምኖርበትን ክፍል ብቻ ከእሳት አደጋ መከላከሉ ብነሳ ለላው እስካልተከላከለ ምን ዋጋ አለው? ከጎኔ ያለው ክፍል በእሳት ከጋየ የነዋ ክፍል እንዴት ታመልጣለች? ቤታችን እንዳለ መቃጠሉ አይቀሬ መሆኑ ነው። እዝያኛው ክፍል የተነሳው እሳት የኔንም ክፍል አይምራትም። አብራ መውደሟ አያደል? ይልቅ የጋራ ቤታችን ከመቃጠሉ አንድ ነገር አንድ ላይ እናድርግ እናድርግ። እሳቱን ተረበርበን አንድ ላይ እናጥፋ። ቤታችንን እናትርፍ። አለበለዚያ የምንገባባት ቤትም አይኖረንም። እኔ ከስደስት ወደ አገሬ የምመለስባትን ቀን በጉጉት እየጥበቅኩ ነው። ውጪ ዕድሜዬም እየገፋ ነው። ትዳርም አልያዝኩም። እዚህ ተበታትነን አንዲት ፋይዳ ሳንፈይድ በታችን መቃጠሏ ነውና አንድ ነገር እናድርግ።

ብለው ተማጽነዋል። ይኸ አባባላቸው በአድማጭ ልብ ገብቶ ሲጎዘጎዝ ሌላ ለጆሮ ብቻ ሳይሆን ለሚያስብ አዕምሮም ስንቅ በሚሆን ማራኪ አባባል ንግግራቸውን ደመደሙት።

> ኢትዮጵያን እንደ የአንድ የአበባ መደብ እንመስላት። የኢትዮጵያው ውበት የተላያዩ አበቦች የሚበቅልባት መደብ ውብ መደብ መሆኗ ነው። የአንድ ዘር ቀለም የአበበባት መድብ ብቻ ብትሆን ምንኛ በደበረችን ነበር። የተተከለባት አበባ ምንኛ አሰልቺ በሆነ ነበር። የኛይቱ ኢትዮጵያ ግን በተለያዩ ብረ ቀለማት ያሸበረቀች ውብ ውብ የአበባ መድብ ናት። እቅፍ አበባ፣ አበባነቱ የሚታወቀው የተለያዩ ቀለማት አንድ ላይ እጅብ ብለው ሕብረት ፈጥረው ሕብረ-ቀለማት ሲፈነጥቁ ነው ይሚማርኩት። አገራችን በተፈጥሮ እንድ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቀች የብዙ ብሔር ብሔርሰቦች አገር ናት። ያ ኩራታችን፣ ያ መመኪያችን፣ ያ መዳኛችን እንጂ መጥፊያችን ከቶም ሊሆን አይችልም። ኑ የአገሬ አበቦች እንትባበር። አንድ ላይ ስንሆን እናምራለን። አንድ ላይ ስንሆን እንጠነክራለን። አንድ ላይ ስንመጣ እንከበራለን። ኦባማ በመመረጡ ደስ ብሎናል። ዳሩ ግን የተመረጠው ለአሜሪካ እንጂ ለኢትዮጵያ አይደለንም። ኦሮሞው ለብቻእው፤ ሰማሌው ልብቻው፤ ቅንጂት ለብቻው፣ ሕብረት ለብቻው ላነጋግርህ ቢለው፣ ከመጤፍ አይቆጥረንም። አንድ ላይ 100፣000 ኢትዮጵያዊ አሰልፈን በአንድ ቀን ካፒታል ሂልን ብናጥለቀለቀው የሚያዳምጥ ጆሮ እናገኛለን። ወዳጅን እናስደስታለን። ጠላትን እናሳፍራለን። ወያኔ ልዩነታችንን ለክፋ ዓላማ ተጠቀመ። ኑ እኛ ደግሞ ያንን ውብ ያደረገችንን የተለያዩ ቀለማት ይቀፍቸውን መደባችንን ለክቡር ዓላም ተጠቅመን እናት አገራችንን እንታደጋት። የጋር የትብብር መድረክ ፈጥረናል (Solidarity Forum)። በያለንበት የየራሳችንን የትብብር መድረክ ፈጥረን ቤታችንን ለመታደግ ቆርጠን እንነሳ!

ይኸ ጥሪ የያንዳንዱን ተሰብሳቢ ልብ ሳበ። ቤቱ በጭብጨባ ተናጋ። ታዳሚ እየተነሳ የልቡን ተናገረ። አቶ ኦባንግን ከልቡ አመሰገነ። ከዚህ በፊት ስብሰባ ላይ አንዲት ቃል ተንፍሰው የማይውቁ ሰዎች ተነስተው ልባቸው እንደተነካ አስረግጠው ወደፊት ተባብረው ለአገራቸው አንድነት እንዲመጥሩ አንድ በአንድ እየተነሱ ቃል ገቡ።

የኢትዮጵያ የሲቢክ ማሕበራት ስብስብ በዩኬም () የተሳካ ስብሰባ ከአቶ ኦባንግ ጋር በመደረጉ ተደስቶ የተደረገለትንም አንዳንድ ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ አመስግኖ ስብሰባው አበቃ።